MCPS ቅጽ 567-3
(የቀድሞው DHHS ቅጽ)
ጃንዋሪ 2020

Montgomery County Department of Health & Human Services (DHHS)
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት
የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

# ለወላጆች/ለሞግዚቶች የማዳመጥ እና የእይታ ምርመራ መግለጫ

ቅድመውዋእለህፃናት/ሄድስታርት ክፍል-ዩኒት
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Rockviille, Maryland 20850

ለእርስዎ ልጅ የትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን-እንድትሆን ጤናማ እይታ እና ማዳመጥ አስፈላጊ ነው። ያልታወቁ እና ህክምና ያልተደረገላቸው የመስማት እና የማየት ችግሮች በልጅዎ የማየት እና/ወይም የመስማት ችሎታ ላይ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል። ለመማር እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር ማየት እና መስማት አስፈላጊ ናቸው። የትምህርት ቤት ልጆች-ህፃናት የመስማት እና የማየት ምርመራ እንደሚደረግላቸው የሜሪላንድ ስቴት ህግ "Maryland Education Law 7-404" ይደነግጋል። ይህንን ህግ በመተግበር ረገድ፣ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሆኑ ተማሪዎች ቅድመሙዋእለህፃናትና ሄድስታርት ጨምሮ የመስማት ወይም የማየት ችግሮች ካሉባቸው የማጣራት ምርመራ ይደረግላቸዋል። በልጅዎ ትምህርት ቤት ስልጠና ያላቸው ባለሙያዎች የማዳመጥ እና የማየት ምርመራ ያደርጋሉ።

ልጅዎ የማጣራት ምርመራውን ካላለፈ(ች)፣ ልጅዎን ወደተፈቀደለት የጤና ተንከባካቢ እንዲወስዱ የሚገልጽ ደብዳቤ በፖስታ መልክት ይደርስዎታል። ልጅዎ ስለ መስማት ወይም የማየት ችግር ህክምና ላይ ከሆነ ያለ(ች)ው፣ ወይም በሃይማኖት መጣረስ ምክንያት የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት ማጣራት እንዲደረግለ(ላ)ት የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ በጽሑፍ ለትምህርት ቤት ነርስ ያሳውቁ።

የእርስዎ ልጅ መነጽር ወይም "contacts" የሚጠቀም-የምትጠቀም ከሆነ በየቀኑ ማድረግ እና በምርመራ ጊዜም ማምጣት አለበ(ባ)ት።

በትምህርት ቤት የሚካሄዱ የማየት ምርመራዎች ሁሉንም አይነት የማየት ችግር ለይቶ ማወቅ አይቻልም ይሆናል። ተጨማሪ ምርመራ ስለሚያስፈልጋቸው የእይታ ችግሮች እና ምልክቶች ወይም የጤንነት ሁኔታዎች የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት ይህንን የሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር-መንግስት የመገናኛ መረብ ይመልከቱ፡- https://www.montgomerycountymd.gov/HHS-Program/PHS/SchoolHealth/HearingVision.html

### የማየት ችግር ያለባቸው ህፃናት ልጆች

የማየት ማጣሪያ ማድረግ ማለት በ optometrist ወይም ophthalmologist የዓይን ህክምና ባለሙያዎች መደረግ ያለበትን አጠቃላይ የዓይን ምርመራ አይተካም። ይበልጥ ተጋላጭነት ባላቸው ቡድኖች፣ የሚከተሉት ህጻናት ልጆች ጨምሮ፣ በ optometrist ወይም ophthalmologist የዓይን ህክምና ባለሙያ አማካይነት አጠቃላይ የዓይን ምርመራ እንዲያደቱ የ "National Center for Children's Vision and Eye Health" ያበረታታል።

- ጤነኛ የማይመስሉ ዓይኖች
- የመስማት/የማዳመጥ ችግር(hearing impairments፣ የአእምሮ ድክመት/ሽባነትcerebral palsy፣ መከፋት/መቆዘም (Down's syndrome)፣ የአእምሮ ዘገምተኛነት/(autism spectrum disorders)፣ የዘገየ አፍ መፍታት/ተብታባነት (speech delay) የመሣሠሉ የነርቭ ህዋሣት እድገት መዛባት
- በታወቀ "eye—diabetes እና rheumatoid arthritis" ምክንያት የጤንነት ተፅእኖ ሁኔታዎች
- የማየት ችግር ያለባቸው ወላጆች ወይም ወንድም/እህት
- ከ32 ሣምንት ባነሰ ጊዜ (ጊዜው ሳይደርስ) የሆነ
- ልጃቸው የማየት ችግር አለበ(ባ)ት ብለው የሚያምኑ ወላጆች/ሞግዚቶች

### የማየት ችግሮች

- Amblyopia, also called lazy eye, is blurry or reduced vision that is not corrected by glasses. ሸውራራ ዓይኖች፣ በቀጥታ ያልሆኑ ዓይኖች ወይም አንድኛው ዓይን ከሌላው በተሻለ ሁኔታ ማተኮር የሚችል የማየት ችግር/amblyopia ሊፈጥር ይችላል። የማየት ችግር/amblyopia ለማከም ይቻላል።
- ለተዛባ እይታ የሚዳርግ የዓይን ውስጥ ችግር/Astigmatism ብዥታ ያለው እይታ የሚከሰተው አሳልፎ የሚያሳይ የዓይን ብሌን ሽፋን/cornea ያልተስተካከለ ቅርፅ ሲኖረው ነው። የተዛባ እይታ ችግር/Astigmatism ያለባቸው ልጆች መነፅር/ኮንታክት ያስፈልጋቸው ይሆናል።
- Farsightedness (hyperopia) occurs when the eyeball is too short for focusing. በቅርበት ያሉ ነገሮች ምስሎች ብዥ ብለው ይታያሉ። የቅርብ ነገሮችን የማየት ችግር/hyperopia በመነፅር/በኮንታክትስ ሊስተካከል ይችላል።
- Nearsightedness (myopia) occurs when the eyeball is too long for focusing በርቀት ያሉ ነገሮች ገፅታ ብዥ ያለ ይሆናል። ሩቅ ነገሮችን የማየት ችግር/Images በመነፅር/በኮንታክት ሊስተካከል ይችላል።
- ሸውራራነት/Strabismus ማለት የተንሸዋረሩ ዓይኖች ወይም አንዱ አይን ከሌላው ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ፡ ሸውራራነት/"strabismus" ካልታከመ በስተቀር "amblyopia" የማየት ችግር ሊፈጥር ይችላል።

ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት ወይም ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ DHHS Head Start Health Coordinator በስልክ ቁጥር 240-777-1645 ይደውሉ።